# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ(ኢሕአፓ)
## *Ethiopian People´s Revolutionry Party(EPRP*

**አለም አቀፍ የፕሬስ ነፃነት ቀን**

ሚያዚያ 25 ቀን 2005 ዓ.ም. 3 May 2013

አርብ ሚያዚያ 25 ቀን 2005 ዓ.ም.(ሜይ 3. 2013) አለም አቀፍ የፕሬስ ነፃነት ቀን 20ኛ ዓመት በመላው አለም የተከበረ ሲሆን ሰላም ወዳድ ኃይሎች የተለያዩ ዝግጅቶችን ለሕዝብ በማሳየትና ለሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላትም የአቤቱታ ጥያቄዎቻቸውን በማቅረብ አክብረውት ውለዋል። ቀኑን ዴሞክራሲያዊ የሆኑ ሀገራት፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና መሰል ተቋማት ጭምርም ዘክረውታል።

አለም አቀፍ የፕሬስ ቀን በየአመቱ የሚከበረው አለምክንያት አይደለም። የነፃ ፕሬስ መኖር የሚያረጋግጠው ጋዜጠኞች ያለምንም ጭንቀትና ፍርሃት የሚያስቡትን፡ የሚሰማቸውን፡ የሚሰሙትን እንዲሁም ምርምር አድርገው የደረሱበትን ዜናዎች በነፃ ለመፃፍና ለማሰራጨት ብሎም ሕዝብ እንዲወያይበት ለማድረግ ያላቸውን ያልተገደበ መብት ሲሆን ይህም ለማንኛውም ሕብረተሰብ ጤናማ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለእድገቶቹም ወሳኝ ነው። ነፃ ፕሬስ የኃሳብ ነፃነት ተግባራዊ ለመሆኑ ዋስትናም መፈተኛም ነው። ኃሳብን ያለምንም ጭንቀትና ፍርሃት በነፃ ለመግለፅ መቻል፤ ዜናን አስመልክቶ ምርምር ማድረግና መለዋወጥ እንደ ምግብና መጠጥ፤ ጤንነት፡ እውቀት መገብየት ሁሉ ሰብአዊ ክቡርነትን የተላበሰ ሕይወት ለመጎናፀፍም አስፈላጊም ወሳኝም ናቸው። ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መብት መኖርና ዋስታናው ዴሞክራሲያዊ በሆነ ሕግ መረጋገጥ ማለት ዘላቂነት ላለው ዴሞክራሲያዊ እድገት ለማገኘትም ዋና መሰረት ነው።

ነፃ ፕሬስ የሀሳብ ነፃነት መብት አልፋና አሜጋው ነው። እውቀትን ለመገብየትና ማናቸውንም ዜናዎች የማግኘት ዋስትናን ለማረጋገጥ የነፃ ፕሬስ መኖር በዋነኛነት የሚጠቀስና ያለምንም ገደብ ተግባራዊ እንዲሆን በሰላም ወዳድ ኃይሎች የሚጠየቅ ነው። የዚህን እውነተኛነት በመገንዘብ ነው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከ 1994 ዓ.ም. ጀምሮ በየአመቱ እንዲከበርና ይህንን አስመልክቶ በነፃው ፕሬስ አባላት ላይ የሚደረጉ ማናቸውም ክትትሎች፤ እንግሎቶች፤ ወከባና ግድያ እንዲቆሙ ጥረት እንዲደረግ ውሳኔውን ያስተላለፈው፤ ባፀደቀው የሰብአዊ መብት ሰነድ ውስጥም በአንቀጽ 19 በግልፅና በማያሻማ አኳኋን እንዲቀመጥ ያደረገው።

ነፃ ፕሬስ በመንግሥትም ሆነ ዴሞክራሲያዊ ባልሆኑ ቡድኖች በግልፅም ሆነ በስውር፤ በግለሰብ፤ በቡድንና በተለይም በአናሳ የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚደረጉ በደሎችን፤ አፈናዎችን፤ ሙስናና ኢፍትሃዊ እርምጃዎችን ለማጋለጥ ሕዝብ እንዲያውቀውና እንዲታረሙ ለማድረግ የሚረዳ ነው። ነፃ ፕሬስ የባለሥልጣናትን የተዛባና ጎጂ ድርጊቶቻቸውን ለማጋለጥና ለሚወስዷቸው ማናቸውም እርምጃዎች ሁሉ በሕግ ተጠያቂነት ያለባቸው መሆናቸውን በማስረገጥ ለሕዝብ ማብራሪያ እንዲሰጡ የአቅሙን ለመወጣት የሚጥር ተቋም ነው። ባጠቃላይ የሃሳብ ነፃነት መኖር ሌሎች መብቶች ሁሉ በዚሁ መሠረት ላይ የሚገነቡና የሚጠናከሩ ናቸው።

ይህ በማንኛውም ሰላም ወዳድ ኃይል ጠቃሚነቱ ከግንዛቤ የገባና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እውቅና ያገኘ መብት ሆኖ ሳለ ግን አሁንም ድረስ በአለም አቀፍ ባሉ በርካታ ሀገራት በተለይም ደግሞ በማደግ ላይ በሚገኙት ውስጥ በነፃ ፕሬስ አባላት ላይ በአገዛዞቹ የጸጥታና የደህንነት ተቋማቶቻቸው አማካኝነት ክትትል፤ ማስፈራራት፤ ማስጨነቅ፡ ደብዛ ማጥፋት፡ ያለውዴታ በግዴታ ለስደት መዳረግና ብሎም የተለያዩ እስከ ሞት የሚያደርስ የኃይል እርምጃ እየተወሰደባቸው ይገኛል።



**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email ESPIC@aol.com**
**Website WWW.EPRP.com**

**EPRP**
**BP 22**
**92270 Bois Colombes**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**

ዛሬ ይህ አለም አቀፍ የነፃ ፕሬስ በሚታወስበት ወቅት የሚተላለፈው መሰረታዊ መልዕክት ይህንን መብታቸውን በመጠቀም ለሕዝብ ዜና ለማቅረብ ከፍተኛ ጥረት በሚያደርጉ የነፃ ፕሬስ አባላት ላይ እየደረሰ ያለው ወከባና ችግር፤ ግድያና እስራት እንዲቆምና ሥራቸውን ለማከናወን ይቻላቸው ዘንድም ተስማሚ የፖለቲካ ምህዳር እንዲገኝ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን በመደገፍና የታሰሩትም ያለምንም ቅደመ ሁኔታ እንዲፈቱ ለመጠየቅ በሚደረገው ትግል ግለቱ እንዲጨምር ሁሉም የየበኩሉን አስተዋፅዖ ለማበርከት ነው።

እይታችንን ወደ ሀገራችን ስናደርግም ከተለያዩ አለም አቀፍ ተቋማት ውስጥ የተገለበጡ አንቀጾችን ሕገ መንግስት ተብየው ውስጥ  አካትቻለሁ ቢልም ወያኔ በተግባር  በዴሞክራሲያዊ ሥርአት ለመመራትና ለመገዛት ፍላጎት የሌለው ነውና ነፃ ፕሬስ ሊኖር አልቻለም።  የዛሬ 21 አመት ወያኔ ሥልጣን በተቀናጠጠበት ወቅት በራሳቸው ጥረት ለማቆጥቆጥ ችለው የነበሩት የነጻው ፕሬስ ክፍሎች  ዛሬ በወያኔ በደረሰባቸው አፈና ጋዜጣቸውና መፅሄታቸው  ደብዛቸው የጠፋ ሲሆን አባላቱ ደግሞ ለሞት፤ ለስደት ተዳርገዋል። በተለይ ከቅርብ አመታት ወዲህ ደግሞ ጠንካራ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችና ተቃውሞዎችን ለማፈንና የነሱን እንቅስቃሴም ሆነ በአገዛዙ ላይ የሚቀርቡ ማናቸውን ትችቶች ለማፈን ይረዳው ዘንድ ያወጀው የጸረ ሽብረተኝነት ሕግ በአንድ በኩል ሥር አቱን የሚተቹ የሱ ተቀጥላ ለመሆን የማይሹ በርካታ ጋዜጠኞችን እያሸማቀቀ ለማፈን፤  በሌላ በኩል ደግሞ ለገነባው ሥርአት ማቆያ እየተጠቀመበት ይገኛል። የነፃ ፕሬስ አባላት የሚንቀሳቀሱት የግዴታ ወያኔ የገነባውን ሥርአት አዳማቂ ለመሆን ሳይሆን የዴሞክራሲ መብታቸውን  በመጠቀም ያመኑበትን ለሕዝብ ለመግለጽና ለማሳወቅ ነው። ስለሆነም የተፃፈበትን ወረቀት ያህል እንኳ ክብደት የሌለውን አንቀፆች ነጋ ጠባ እየጠቀሱ በጋዜጠኞች ላይ መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ መንዛትና ማዋከብ እንዲሁም ዘብጢያ ማውረድ በምንም መንገድ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም።

በመሆኑም አለም አቀፍ የፕሬስ ነፃነት በሚዘከርበት ወቅት በሀገራችን የነፃ ፕሬስ አባለትን መታሰር አጥብቀን የምንቃወመውና የምንኮንነው ድርጊት መሆኑን እንገልጻለን፡፡ አሁንም ደግመን ደጋግመን የምንለው በሽብርተኝነት ስም ዜጎችን ማሰር መቆም ያለበት መሆኑንና  በአገዛዙ ላይ የሰላ ትችት ማቅረብ፤ የአገዛዙን ደባ ማጋለጥና ሕዝብ እንዲያውቀው ማድረግ ሽብርተኝነት ሳይሆን ሀገር ወዳድነትና ለሕዝብ ቀናኢነት መሆኑን አገዛዙ እንዲገነዘብ ነው። በመሆኑም የታሰሩ የነፃው ፕሬስ አባላት በአስቸኳይ እንዲፈቱ  መጠየቅ አግባብነት ያለው ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም ሰላም ወዳድ ኃይልና ለሕዝብ ቀናኢነት ያለው ሁሉ የግዴታም ግዴታ ነው። ጋዜጠኞችን ልማታዊና ልማታዊ ያልሆኑ እያሉ መከፋፈል ወንጀል  ከመሆኑም በላይ አገዛዙ ከምዕራቡ ወደ ምስራቁ፡ ከሰሜን ወደ ደቡብ በዘለለና አቋሙን በሥልጣን ለመቆየት እንዳመቸው በቀየረ ቁጥር ጋዜጠኞች የአገዛዙን ፈለግ እንዲከተሉ መጠበቅና ማስገደድ የአምባገነን አገዛዝ ባህርይ ነው።

ስለ ነጻው ፕሬስ ጥሩም ሆኑ መጥፎ ፈራጁ ሕዝብ እንጂ የወያኔ አገዛዝ  ጨርሶ ሊሆን አይችልም። በነፃ ፕሬስ ላይ በሚወጡ መጣጥፎች ምክንያት ሕዝብ እርስ በርሱ ይጣላል፡ ለሁከት ይዳረጋል ብሎ ማሰብ የሕዝብን የማመዛዘን ችሎታ አለመገንዘብና ሁሉን ነገር እኔ አውቅልሃለሁ የሚል መሰሪ ደዌ የተጠናወተው አምባገነን ብቻ ነው። በወቅቱ በአዲስ አበባ ይሰራጩ የነበሩ የነፃው ፕሬስ እትሞች በቆሻሻነት ተወግዘው ወደ ትግራይ እንዳይገቡ መደረጋቸው የሚታወስ ነው። ታዲያ ዛሬ ወያኔዎች በድንገት ዴሞክራሲያዊ ሆነው የነፃ ፕሬስ መብት አክባሪ ሊሆኑ የሚጠበቅ አይደለም። ነፃ ፕሬስ የተለያዩ የሕዝብ አስተያየቶች፡ ምኞቶችና ፍላጎቶች የሚስተናገዱበት፤ በዚህም የውይይት መድረክ ሆኖ የሚያገለግል እንጂ በአገዛዙ በልማት ሥም በተቀየሰ መስመር እንዲሄድ ለማድረግ መጣር መብትን መደፍጠጥ እንጂ በሌላ በምን ሊተረጎም አይችልም።  በሀገራችን በአሁኑ ወቅት እየተስተዋለና እየተገበረ ያለው ይህ ነው። „አገዛዛችንን አትጥሉብን፡ ያወጅነውን ሕግ አትጣሱብን፡ የኛ የዴሞክራሲ ግንዛቤ ብቻ ተቀበሉ፡ እኛ ከወስንነው የሙያ ስነምግባር አሰራር ከወጣችሁ ወዬውላችሁ፡ የኛን ተግባር ብቻ እያዳነቃችሁ ጻፉ“ ማለት በመድበላዊ ዴሞክራሲ ጠላቶች የሚነዛ የጠነባ የአምባገነንነት ጠባይ ነውና በፍፁም  የሚወገዝ ነው።



EPRP
P.O.BOX 73337
Washington DC, 20056
USA

Email ESPIC@aol.com
Website WWW.EPRP.com

EPRP
BP 22
92270 Bois Colombes
France

Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645

ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ኃሳብን በነፃ የመግለፅ መብትና እንዲከበርና ከማናቸውም የፖለቲካ ኃይል ጣልቃ ገብነት የተላቀቀ ለሕሊናውና ለሕዝብ ተጠያቂ የሆነ ነፃ ፕሬስ እንዲኖር፤  አባላቱም ሕዝብ የማወቅ መብት አለው በሚለው መርህ ሥር  ሥራቸውን በነፃነትና ደህንነታቸው ሳይደፈር የሚያከናውኑበት የፖለቲካ ምህዳር እንዲፍጠር ይታገላል። የመገናኛ ዘዴዎች በከፍተኛ ደረጃ ባደጉበት ባሁኑ ወቅት ነፃ ፕሬስን በተለያዩ ደረጃዎች ለማፈን መጣር  አባላቱንም በሽብርተኝነት ሥም መክሰስና ዘብጢያ ማውረድ ከፍተኛ ወንጀል ነው።

ነጻ ፕሬስ ዝም ብለን ስለተመኘነው በተአምር የሚመጣ አይደለም፣ ሁሉም ዜጎች ከወያኔ የማጭበርበሪያና የማወናበጃ ቀለበት በመውጣት አመቺ መስሎ በታያቸው ዘዴ ተደራጅተውና  ተመሳሳይ ሃሳብ ያላቸው በርካታ ሰዎችንም አደራጅተው በተናጠልም ሆነ በቡድን ይህን የነፃ ፕሬስ ጠላት መሆኑን በተደጋጋሚ ያስመሰከረ የወያኔን አገዛዝ ለማስወገድ ጥረት ማድረግ አለባቸው። ነጻ ፕሬስ ሲኖር ነው በሀገራችን ሁሉም  በእኩልነት ተከብረው የሁሉም መሰረታዊ መብቶች ባለቤት ሊሆኑ የሚችሉት። ይህ ነው በዛሬው ቀን በሰላም ወዳድ ኃይሎች እየተላለፈ ያለው መልዕክት።

በኢሕአፓ  እምነት አማራጭ የሌለውንና በተፈጥሮ የታደልነውን ነጻነታችንን ለማስከበር የምንችለው ወያኔ እንደ ምጽዋት እስጣችኋለሁ በሚለው መንገድን  በመከተል ወይንም ደግሞ ከተለያዩ አለም አቀፍ ሰነዶች ገልብጦ በሕገ ወያኔነት ያወጀውን ሕገ አገዛዙን አምኖ በመቀበልና በማክበር ሳይሆን ማናቸውንም አይነት የትግል ስልቶችን በመጠቀም በቆራጥነትና በተባበረ ትግል በመሰማራት ነው። ይህ ስኬታማ ሲሆን ያኔ ጋዜጠኞቻችን አለም አቀፍ የፕሬስ ነፃነት ቀንን ከወዳጆቻቸው ጋር በመሆን በሰላም ያከብሩታል።  እኛም በትግላቸው ወቅት ከጎናቸው እንደቆምን ሁሉ በሰላሙም ጊዜ ቀኑን አብረን በጋራ እናከብረዋለን። ይህ ደግሞ የብዙሃኑ ቀና ምኞት ነውና ለተግባራዊነቱ ሁሉም ሀገር ወዳድ ኃይል እንዲተባበር የከበረ ጥሪ እናቀርባለን።

ነፃ ፕሬስ በወያኔ መቃብር ሕልውና ያገኛል!!

የታሰሩ የነፃ ፕሬስ አባላት በአስቸኳይ ይፈቱ!!



**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email [ESPIC@aol.com](mailto:ESPIC@aol.com)**
**Website [WWW.EPRP.com](http://WWW.EPRP.com)**

**EPRP**
**BP 22**
**92270 Bois Colombes**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**